# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

# Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

**ነሐሴ 26 ቀን 2005 ዓ.ም.**

## ነሔሴ 26-- ኢሕ አፓ ከታወጀ 38 ዓመት

ኢሕአፓ የዛሬ 38 ዓመት ህልውናውን ሲያውጅ ( የተመሰረተው በሚያዝያ 1964 ቢሆንም) ከደርግ አገዛዝ ጋር ፍልሚያ ለገባው የኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ የምስራች ነበር ። ቀደም ብሎ አቅም ኑሮት ትግሉን ሊመራና ሕዝባዊ እንቅስቃሴውን ሊከላከልና ትግሉን ሊመራ የሚችል ኃይል ባለመከሰቱ የየካቲት 66ን አብዮት ድል ምርጥ መኮንኖች ሊቀሙና ወታደራዊ አምባገነናዊ አገዛዝ ሊመሰርቱ ችለው ነበር። ህዝብ ሞግዚት አይፈልግም፤ ሥልጣን ለሕዝብ ብሎ የተነሳው የኢትዮጵያ ህዝብ በኢሕአፓ ይፋ መወጣት የፈነደቀው ድርጅቱ ለትግሉ ጠንካራ ክንድ እንደሚሆነው በመረዳትም ነበር ።

ነሐሴ 26/1967 ዓ.ም. በሚያስደንቅ ሁኔታ መርሐ ግብሩን/ፕሮግራሙን/ በመላ ኢትዮጵያ ያሰራጨውና በዚህም ስምሪት አንድም እንኳን አባል ለእስር ያልተዳረገ መሆኑ ደግሞ በራሱ ለድርጅቱ ችሎታና አደረጃጀት ምስክር ሆኖለታል ። ኢሕአፓ ከታወጀ በኋላ የሕዝብ ትግል ምን ያህል እንደተጠናከረ ደግሞ ዘጋ ሁሉ የሚያውቀው ነው። በርግጥ ያኔ የነበሩት ጠላቶቹና የዛሬዎቹም ተደምረው የኢሕአፓን ታሪክና ገድል በመጥፎ ሊያቀርቡና አዲሱን ትውልድ ሊያደናግሩ መሞከራቸው የሚታይ ነው ። ኢሕአፓ ግን መጻፍ መናገር ብቻ ሳይሆን በትግሉ ሜዳ ተሰማርቶ ለሀገራችንና ለሕዝባችን ይህ ነው የማይባል መስዋዕትነት የከፈለና እስከዛሬም ህልውናውን ጠብቆ እየታገለ ያለ ድርጅት ነው ። ትግል ሰርግ አይደለምናም፤መስዋዕትነትም የግድ ነውና--ዛሬም ሕዝብ ወያኔን ሲታገል እንደሚታየው ሁሉ--ብዙ ሕይወት ለትግሉ ተግብሯል። ይህንንም ድርጅቱ ሕዝብ አስጨረሰ በሚል ሊመዘግቡ የሚጥሩት ወንጀለኞችና ጠባቦች ከታሪክ የተጣሉ መሆናቸውንም ማወቅ ከባድ አይደለም ። ዛሬም ቢሆን ወያኔን ከስልጣን ለማስወገድ ብዙ መስዋዕትነትን ጠያቂ መሆኑ እየታየ ነውና ።

ኢሕ አፓ የሕዝብ አለኝታ ነው ሲባል ገና ከምስረታው የተነገረው በረጅምና መራራ ትግል የተረጋጋጠ ነው። ትላንትም ዛሬም በድርጅቱ ውስጥ ብቅ የሚሉ አፍራሾች አንድነቱን ቢፈታተኑም ከቶምና መቼም ሊያፈርሱት አልቻሉም ። ትላንትም ዛሬም አረመኔ አገዛዞች ሊያወድሙት አስከፊ እመቃና አፈና ቢያካሂዱበትም፤ አባሎችና አመራሮችንም ቢገድሉበትም፤ የለም ሞቷል ተኗል ብለው ቢቧርቁበትም

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel 202-291-4217 fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
website: WWW.EPRP.COM

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

ኢሕአፓ በነሐሴ 26/1967 ያወጀውን ህልውናው ጠብቆ፤ ለሕዝብ የገባውን ቃል ኪዳን አክብሮ እስከዛሬ በቆራጥነት የኢትዮጵያ ኃይልና ተገን ሆኖ እየታገለ ነው።

በርግጥም የሚያኮራ ታሪክ!

የኢሕአፓ አንድነትና ቃል ኪዳን የተጠበቀ ነው!

ትግላችን ይቀጥላል !!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel 202-291-4217 fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
website: WWW.EPRP.COM

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France